በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መልካም ፍሬ ማፍራት


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*<u>ቦታ፡-</u>* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## መጋቢት ፳፪ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

# መልካም ፍሬ ማፍራት

- “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።” ***ማቴ 7፡16-20።***
- በዚህ በተቀደሰው ሳምንት ከሚገኘው የተቀደሰ አገልግሎት በረከት ተሳታፊ ለመሆን ቁርጥ ባለ መንገድ ራስን መመርመር አስፈላጊ ነው። ልባችንንም በመመልከት ምን ዓይነት ፍሬ እያፈራን እንደሆነ ራሳችንን መጠየቅ ተገቢ ነው።
- የወይን ግንዱስ ቅርንጫፎችስ መልካም ፍሬን ለማፍራት ጥንካሬ አላቸው?
- አንድ ሰው ራሱን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊጠይቅ ይችላል?
    - ዘወትር ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና መጸለይ የየዕለት ተግባሬ ነው?
    - የምጾመው መንፈሳዊ ጥንካሬን ፈልጌ ነው?
    - ቅዳሴ በማስቀደስ የተነበቡትን ምንባባት ከማስታወስ ጋር በየዕለቱ የሚነበበውን ስንክሳር ቤተሰባዊ ምክክር ለማድረግስ እጠቀምበታለሁ? በተቀደሱት የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት በማመን ተሳትፎ እናደርጋለን?ጌታዮ ስለኔ ኃጢአት እንደ ሞተልኝ የዘላምን ሕይወትንም ይሰጠኝ ዘንድ ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሳልኝ አስተውላለሁን?
- ለዚህ የሰጠነው መልሳችን አዎ ከሆነ በእርግጥም ፍሬአችን ጠንካራ ባስተማረን መሠረት ለጌታችን ያለን መንፈሳዊ መሥዋትነት የቀናና ቅዱስም ነው ማለት ነው።

# መልካም ፍሬ ማፍራት

- በማስከተልም አንድ ሰው ራሱን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ሊፈልግ ይችላል?
    - መንፈሳዊ ፍሬዎችን እያፈራሁ ነው?
    - ከቅዳሴና ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውጪ ከሌሎች ጋር ባለኝ ግኑኝነት የሚታየው ምግባሬ በውስጥም ሆነ በውጭ ክርስቲያን መሆኔን ይመሰክራል?
    - የአገልግሎቱ ዓይነት ምንም ይሁን ምን ዘወትር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እሰጣለሁ?
    - ቅዳሴ ማስቀደስ የማይችሉ ሕሙማንንና ሽማግሌዎችን እንዲሁም አቅመ ደካማዎችንስ እጎበኛለሁ?
    - ከእኔ ያነሰ ዕድል ያላቸውንስ እረዳለሁ?
    - በቤተ ክርስቲያን እንግዳ የሆኑትን የፍቅር ግብዣ  ለመጋበዝ በሬን እከፍትላቸዋለሁ?

ወይም

- ከቤተሰብና ከጓደኞቼ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር አለመግባባትን ወይም ክርክርን እገጥማለሁ?
- ለሌሎች ክፋት አለኝ፣ ኩራትስ ይሰማኛል?
- ስለሌላው ሰው የተነገረኝን ነገር የሰማሁት ማስረጃ ሳይኖር ወይም እኔም ማረጋገጫ ሳይኖረኝ በፍርደ ገምድልነት እፈርድበታለሁ? አንዱን ወገን ለማራቅ በሚፈጠር ክርክር ውስጥ እወግናለሁ? ሥራዬ፣ ጥናቴ፣ ማኅበራዊ ሕይወቴ ከአምላኬ ከአየሱስ ክርስቶስ በፊት ይሆን?
- በተግባር የተደረጉ ነገሮችን ሐሳባቸው ወይም መሻታቸው ምን እንደሆነ ሳላውቅ በሐሰት አንድን ነገር በተሳሳተ መንገድ እንዳምን ያደርገኛል?

# መልካም ፍሬ ማፍራት

- ያለአግባብ መከሰስንና የተዛባ ፍርድን አስመልክቶ ለመንፈሳውያን ምሳሌ የሚሆነን ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ነው፡፡
- ቅዱስ ኤፍሬም የእመቤታችንን ምስጋና የደረሰ የሐዲስ ኪዳንን መጽሐፍ በጻፈው በቅዱስ ያዕቆብ የተጠመቀ ነው፡፡ ቅ. ኤፍሬም ሳይገናኙ በስሙ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ የሚያውቀው ቅዱስ ነበር፡፡
- ቅዱስ ኤፍሬም ብዙ ተአምራትን አድርጓል፣ በርካታ ትምህርቶችን ጽፏል ቅዱስ ሰው መሆኑም በስፋት ተቃባይነት ያገኘ አባት ነበር፡፡
- ይሁን እንጂ ጥንቃቄ በተሞላበት ገዳማዊ ሕይወቱና ራሱን በትሕትና በሚገልጥባቸው ኑሮው በአረጋውያን ያላግጣል ተብሎ በሐሰት ተከሰሰ፡፡ ቅዱስ አፍሬም ከወጣትነቱ አንስቶ የሚሰቃይበት የጀርባ ሕመም ነበረበት፡፡ በዚህም የተነሳ በዕድሜ መግፋት የተነሳ እንደሚያደርጉት አረጋውያን መነኮሳት ሕመሙን ሊቋቋመው ስላልቻለ ከዘራ ይዞ ይጓዝ ነበር፡፡
- አንዳንድ መነኮሳትም ቅዱስ ኤፍሬም ከዘራ ይዞ በመሄድ በአረጋውያን ያላግጣል ብለው በሐሰት ፈረዱበት፡፡
- እነዚህ መነኮሳትም የራሳቸውን ግምትና ፍርድ በገዳሙ ውስጥ ላሉት መነኮሳት ነገሩ፡፡
- እውነትን ለመረዳት ለፈለጉ ጉዳዩ ሩቅ ባይሆንም ቅዱስ ኤፍሬም ግን ስለራሱ አልተከራከረም፡፡ ይልቁኑ ሁሉም እንዲመለከቱት አድርጎ በመነኮሳቱ ሁሉ ፊት በገዳሙ ውስጥ ከዘራውን በመሬት ውስጥ ተከላት፡፡ ይህች ቅዱስ ኤፍሬም የተከላትት በትርም በማግስቱ አብባ አበባ አፈራች፡፡

# <u>መልካም ፍሬ ማፍራት</u>

- እስከዛሬም ድረስ በሶርያ በምትገኘው በአል ሱርያን ገዳም ውስጥ እንደ ሃይማኖት ምስክርና በሐሰት በሌላው ስለመፍረድ ማስጠንቀቂያ ሆና እያበበች ትኖራለች፡፡
- ይህች ያበበች በትር የመታዘዝ ዛፍ ተብላ ስትጠራ በትንቢትም ፍሬ ታፈራለች፡፡
- ይህች ያበበች በትር ዛሬም ከጥንቱ የአል ሱርያን ገዳም ዋሻ ቀጥሎ ትገኛለች፡፡

- ቅዱስ መጽሐፍ ፍሬ ስለምታፈራዋ የበለስ ዛፍ ምሳሌዎች ይልቁንም መንታ ሕይወት ወይም ምላስን ምሳሌ በማድረግ ይዞ ያስነብበናል፡፡
- የበለስ ዛፍ በቅድስት አገር በመላ የሚገኝ ሲሆን የቀደሙት ሰዎች ምግባቸው ነበር፡፡ በለስ ጣፋጭ፣ ተወዳጅና ከወይን ተክል ጋር አብሮ የሚተከል ነበር፡፡
- ታላቁ የበለስ ዛፍ ቅጠል የአዳምና ሔዋንን ራቁትነታቸውን የሸፈነ ሲሆን ናትናኤልም "መጥተህ እይ" ተብሎ በቅዱስ ፊሊጶስ በተጠራ ጊዜ ከጸሐይ የተከለለበት ጥላ ነበር፡፡ *<u>ዮሐ 1፡46፡፡</u>*
- በለስ "በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ፡፡ ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ መጣ፥ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም፡፡ መልሶም፡፡ ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ከአንቺ ፍሬ አይብላ አላት፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ሰሙ፡፡ " እንደ ተባለው በቀጥታ ተቀጥፎ መበላት የሚችል ነው፡፡ *<u>ማር 11፡12-14፡፡</u>*

# መልካም ፍሬ ማፍራት

- ፍሬን ማፍራት በእግዚአብሔር ላለን እምነት መሠረት ነው፡፡
- "የወይን አትክልት ሠራተኛውንም፡፡ እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም፤ ቍረጣት፤ ስለ ምን ደግሞ መሬቱን ታጐሳቍላለች? አለው፡፡" _ሉቃስ 13:7፡፡_
- በቤተ ክርስቲያንን ትተው ዓለማዊውን መንገድ በመከተል ለሚጓዙ ይኽን የመሰለ ነገር ይገጥማቸው ይሆን? ቅዱስ ያዕቆብ ይህን የበለጠ ለማጉላት "ወንድሞቼ ሆይ፥ በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣም፡፡" _ያዕ 3:12፡፡_
- በርግጥ ይህ እስከዛሬ ድረስ ከቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ የሆነ ጠባይ ይዘው የሚጸልዩ ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንም የሚሳተፉትን የሚጠቁም ነው፡፡
- ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሰው  ቤተ ክርስቲያን የመከታተል ዓለማው ይልቁኑ በዚህ ወቅት በንስሐ ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ለመሳተፍ ካልሆነ ምክንያቱ ምንድር ነው ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡
- ጌታችን ልባቸው ለጨለመ በጎ ሥነምግባር ለጎደላቸው በሌሎችም ስለሚፈርዱ የሰው እምነት ሲገለጥ መልካም ፍሬው ተፈላጊ እንደሆነ አስተምሯል፡፡
- በፍሬ አልባነቷ የተነሳ የበለስ ዛፍ ጠውልጋ እንደተገኘች መንፈሳዊ ፍሬ የሌላቸውስ ምን ይሆኑ ይሆን?

# <u>መልካም ፍሬ ማፍራት</u>

- ቅዱስ ያዕቆብ ሁላችንንም ትሑታን፣ ሌሎች የፈረዱብንን ስለመተው፣ የዓለም የሆነውንም መንገድ በጽድቅ እንድንቋቋም አስተምሮናል፡፡ “ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ፦ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል፡፡” <u>*ያዕ 4፡6፡፡*</u>

- ከጥፋታችን መመለሳችንንና መዳናችንን የሚሰብኩትን ተመልከቱ፡፡
- ሌላውን የሚወቅሱትንና የሚከሱትን ሰውንም ከሌላው ነጥሎ ከመግፋት የሚፈልጉትን ተመልከቱ፡፡
- ሰላምን ከሚሰብኩት ጋር ነን ወይስ መራርነትን ከሚነግሩን?
- ፍሬ ከሚያፈሩት ጋር መሆናችን ያስደስተናል ፍሬ ከማያፈሩት ጋር መወዳጀታችን?
- ጌታችን እንድታብብ ዕድል ያልሰጣትን የጠወለገች በለስን ነን?
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “የበለስ ዛፍ ሰፋፊ ቅጠሎች ሰፊውን መንገድ የሚገልጽ ሲሆን አዳምና ሔዋን በበለስ ዛፍ ሊሸፍኑት የሞከሩትን ኃጢአት ያስታውሰናል፡፡” ብሎናል፡፡
- የውጪው ገጽታችንና የውስጡ ሰውነታች እነዲያድግና ፍሬን እንዲያፈራ ባለቤቱ መድኃኔዓለም ይረዳን ዘንድ እንለምነው፡፡

- ለሥላሴ ክብር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን፡፡

ይቆየን።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።